ዘአትናቴዎስ ፡ ም ፡ ፳፫ ።

፲፰፡ ወዘይቤ ፡ እስመ ፡ ሥጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ እምሰማይ ፡ ወአኮ ፡ ውእቱ ፡ እማርያም ፡ ድንግል ፡ አው፡ ዘይቤ ፡ ተመይጠ ፡ መለኮት ፡ ለከዊነ ፡ ትስብእት፡ አው ፡ ተቶስሐ ፡ ምስሌሁ ፡ አው ፡ ተወለጠ ፡ አው፡ ዘይብል ፡ መለኮቱ ፡ ለወልድ ፡ ሐመ ፡ አው ፡ ዘይቤ፡ ለሥጋ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢይሰግድ፡ ሎቱ ፡ እስመ ፡ ሥጋ ፡ ሰብእ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ፡ ወኢይቤ ፡ እሰግድ ፡ ሎቱ ፡ እስመ ፡ ሥጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ወለእለኒ ፡ ይብሉ ፡ ከመዝ ፡ ታወግዞሙ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ሰሚዓ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያሁ ፡ ለወልደ ፡ እግዚአብሔር፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኵሉ ፡ ዘይሜህረክሙ ፡ ካልአ ፡ እምዘመሀርናክሙ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ። ገላ ፡ ፩ ፡ ፯—፲ ።

ክፍል ፡ ፱

፲፱፡ ወከዐበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሐዋርያዊ ፡ በውስተ ፡ ድርሳኑ ፡ ዘደረሰ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ እሉሂ ፡ ካልአን ፡ በኡ ፡ ውስተ ፡ ሕፀተ ፡ ሃይማኖት ፡ በእንተ ፡ ተኃሥሦቶሙ ፡ ወተሰዕሎቶሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ በአይ ፡ አርአያ ፡ ወአይ ፡ አምሳል ፡ ይከውን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰብአ ።

፳፡ ወህየንተ ፡ ትሥጉት ፡ ፈጠሩ ፡ ሎሙ ፡ ፈጠራ ፡ ወይቤሉ ፡ እስመ ፡ እግዚእ ፡ ኀደረ ፡ ውስተ ፡ ብእሲ ፡ ወህየንተ ፡ ተዋሕዶተ ፡ መለኮት ፡ ወትስብእት ፡ ወኅብረት ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ፈጠሩ ፡ ግብረ ፡ እንለ ፡ እመሕያው ፡ ህየንተ ፡ ፩ዱ አካል ፡ ዘእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተአመኑ ፡ በ፪ኤ ፡ አካል ፡ ወበ፪ኤ ፡ ህላዌ ፡ ወበ፪ኤ ፡ ገጽ ፡ ወህየንተ ፡ ዘይደሉ ፡ አሚን ፡ በሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ አምኑ ፡ ረቢዖሙ ፡ በግብር ፡ ዘኢከነ ፡ ሠናየ ።

፳፩፡ ወዝ፡ ዕልወት ፡ ዘኢይደሉ ፡ ወዘኢይበቍዕ ፡ እስመ ፡ አስተአኀዙ ፡ ብእሴ ፡ ምስለ ፡ አምላክ ፡ ወረሰይዎ ፡ ለገብር ፡ ምስለ ፡ እግዚእ ፡ ወኍለቁ ፡ አካለ ፡ ራብዓየ ፡ ነኪረ ፡ ምስለ ፡ አካላት ፡ እለ ፡ ኢተፈጥሩ ።

፳፪፡ ወበዕልወቶሙ ፡ ይዌስኩ ፡ ውስተ ፡ ሥላሴ ፡ ካልአ ፡ አሐደ ፡ አካለ ፡ ፍጡረ ፡ እምድኅረ ፡ ኵሎሙ ፡ መናፍስት ፡ ነባብያን ፡ ወይሰግዱ ፡ ረቢዖሙ ፡ ህየንተ ፡ ሥላሴ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፱ና ፳ ። ፬ ፡ ፩ ። ፪፡ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፯—፲፱ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፩—፲፫ ።

፳፫፡ ወእሙንቱ ፡ ርጉማን ፡ ወርጉመ ፡ ይኩን ፡ ዘይተሉ ፡ ትምህርቶሙ ፡ ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፵፩ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፬—፳፪ ።

ዘአትናቴዎስ ፡ ም ፡ ፳፫ ።

፲፰፡ የጌታችን ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ከሰማይ ፡ እንደ፡ ተገኘ ፡ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ እንዳልተገኘ ፡ አድርጎ ፡ የሚናገረውን ፤ ወይም ፡ መለኮት ፡ ሥጋ ፡ ወደ ፡ መሆን ፡ ተለወጠ ፤ ወይም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተቀላቀለ ፤ ወይም ፡ ተለወጠ ፡ ወይም ፡ ወልድ ፡ በባሕርዩ ፡ ታመመ ፡ የሚለውን ፤ ወይም ፡ መለኮት፡ ያልተዋሐደው ፡ የዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ሥጋ ፡ ነውና ፡ ጌታችን ፡ ለተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ አልሰግድለትም ፡ የሚለውን ፤ የጌታችን ፡ ሥጋ ፡ አምላክ ነውና ፡ እሰግድለታለሁ ፡ የማይለውን ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ የሚሉትን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሾመው ፡ ሐዋርያ፡ እኛ ፡ ካስተማርናችሁ ፡ ሌላ ፡ ትምህርት ፡ የሚያስተምራችሁ ፡ ሁሉ ፡ የተወገዘ ፡ የተለየ ፡ ይሁን ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ይዛ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታወግዛቸዋለች ፡ ትለያቸዋለች ። ገላ ፡ ፩ ፡ ፯—፲ ።

ክፍል ፡ ፱ ፡

፲፱፡ ይህ ፡ ሐዋርያዊ ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ በተናገረበት ፡ ድርሳኑ ፡ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እሊህ ፡ ሌሎችም ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ጉድለት ፡ ገቡ ። በምን ፡ አርአያ ፡ በምን ፡ አምሳል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ይሆናል ? ፡ ብለው ፡ ስለመመራመራቸው ፡ ስለመከራከራቸው ።

፳፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ስለማለት ፡ ፈንታም ፡ ራሳቸውን ፡ ለማጉዳት ፡ ልበ ፡ ወለድ ፡ ነገርን ፡ ፈጥረው ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰው ፡ አደረ ፡ አሉ ፤ መለኮትና ፡ ትስብእት፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ተዋሐዱ ፡ ስለ ፡ ማለት ፡ ፈንታ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ነገርን ፡ ፈጥረው ፡ ተናገሩ ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ስለማለት ፡ ፈንታ ፡ ሁለት ፡ አካል ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፤ ሁለት ፡ ገጽ ፡ ብለው ፡ አመኑ ፤ በሦስቱ፡ አካላት፡ ስለማመን፡ ፈንታም፡ሊያምኑበት፡ሊያስተምሩት፡ በማይገባ፡ ሥራ ፡ አራት ፡ ብለው ፡ አመኑ።

፳፩፡ ይህም ፡ የማይገባ ፡ የማይጠቅም ፡ ክሕደት ፡ ነው ፡ ፍጡርን ፡ ከፈጣሪ ፡ ጋር ፡ አቈራኝተዋልና ፡ ተገዥንም ፡ ከገዥ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አድርገዋልና ፡ ካልተፈጠሩ ፡ አካላት ፡ ጋር ፡ ልዩ ፡ አራተኛ ፡ አካል ፡ አለ ፡ ብለዋልና ።

፳፪፡ በክሕደታቸው ፡ በሦስቱ ፡ አካላት ፡ ላይ ፡ ከመላእክት ፡ በኋላ ፡ የተፈጠረ ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ይጨምራሉና ፡ ሦስት ፡ ስለማለት ፡ ፈንታ ፡ አራት ፡ ብለው ፡ ይሰግዳሉ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፱ና፳ ። ፬ ፡ ፩። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፯—፲፱ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፩—፲፫ ።

፳፫፡ እነዚህም ፡ የተረገሙ ፡ ናቸው ፡ ትምህርታቸውንም ፡ የያዘ ፡ የተረገመ ፡ ነው ። ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፵፩ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፬—፳፪ ።

